# ፌደራላዊ ስርአቱ የችግሮች መፍትሄ እንጂ

# ምንጭ አይደለም

ስሜነህ 02-24-17

ፌደራላዊ ስርአት አግላይና የዴሞክራሲ እጦት ምንጭ ነው የሚሉ ዛሬም ብዝሃነት በአንድ ሃገር የኢኮኖሚና የፖለቲካ እድገት ላይ አንዳች ሚና እንደሌለው ይልቁንም አቀርቋዥ እና የአምባ ገነኖች መፈልፈያ ማሽን እንደሆነ የሚከራከሩ አሉ፡፡ እነዚህ ሃይሎችን ጨምሮ ለቡድን መብት ቦታ መስጠት አይገባም የሚለው አስተሳሰብ አቀንቃኝ የሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች ብዝኃነትን መሰረት ያደረገ ስርአት የዘረጉ ሃይሎችን ለአናሳ ብሔሮች ጉዳዩ ከአመጋገብና አለባበስ ባህል ያልዘለለ ነው ሲሉ ቦታ ሊሰጧቸው እንደማይገባ ይወቅሳሉ፡፡ ይሁንና ጠንካራ የባህል ተሟጋቾች የሆኑ እንደ ዊል ኪሚልካና ቻርለስ ቴይለር ዓይነት ምሁራን ኅብረ ብሔራዊ የአስተዳደር ሥርዓት በአንድ አገር ከአንድ በላይ ማንነቶች እንዳሉ ዕውቅና በመስጠት የተገለሉ ቡድኖች፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያኙ እና የዲሞክራሲያዊ ስርአት ዋና መገለጫ የሆነው እኩልነት እንዲገነግን ምክንያት ይሆናል ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ ኅብረ ብሔራዊ የአስተዳደር ሥርዓት ላይ በርካታ ምርምሮችን የሠሩፍ አንቶኒ ስሚዝ የተባሉ ምሁር ዘመኑ የብሔር ማንነት ያንሰራራበት እንደሆነ በመግለጽ ከላይ የተመለከቱት እና ከብዝሃነት ተቃራኒ የሆኑ ርዕዮተ ዓለሞች ግምት እንዳልሠራ ያረጋግጣሉ፡፡ አሁን ሊበራል መንግሥት ራሱ የቡድን ፍላጎትን ገሸሽ ማድረግ እንደማይችል በተለይ ከትራምፕ መምጣት ወዲህ በስፋት እየተስተዋለ ነው፡፡ የተከፋፈሉ ማኅበረሰቦች ያሉባቸው አገሮች ውስጥ ማኅበረሰቦች ራሳቸውን በመደብ፣ በፆታ ወይም በሲቪል ማኅበራት አደራጅተው መንቀሳቀስ ጀምረዋል፡፡ ማንነት ወሳኙ የንቅናቄ መሣሪያ ሆኖ እያገለገለም ይገኛል፡፡ አሁን በሊበራሉ ዓለም ራሱ አዲስ አመለካከት ብቅ ያለ ሲሆን፣ የቡድንና የግለሰብ መብቶች ጎን ለጎን ያሉና ሊከበሩ የሚችሉ ናቸው በሚል የሚከራከሩ ሃይሎች አስተሳሰብ የበላይነትን እያገኘ ይመስላል፡፡ በአጠቃላይ ግን ሁለት ዓይነት የፌዴራል ሥርዓቶች አሉ፡፡ አሜሪካ፣ ጀርመንና ኦስትሪያ የሚከተሉት አካባቢያዊ ፌዴሬሽን አለ፡፡ የዚህ ዓይነት የፌዴራል ሥርዓት ዋነኛ ዓላማ ሥልጣን ከአንድ ማዕከል ወደ ተለያዩ ማዕከሎች እንዲሠራጭ ማድረግ ነው፡፡ ክልሎች አካባቢያዊ አስተዳደሮችን መሠረት አድርገው እንዲዋቀሩ ይደረጋል፡፡ ‘ኔሽን ስቴት

ፌዴሬሽኖች' በመባልም ይታወቃሉ፡፡ ምክንያቱም በፌዴራል ደረጃ አብላጫ ድምፅ የሚኖረው ብሔር በክልልም ደረጃ ተመሳሳይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ በሌለ በኩል እንደ ኢትዮጵያና ህንድ ያሉ ፌዴሬሽኖች ዓላማ ሥልጣንን ከማሠራጨት በተጨማሪ የብሔሮችን ጥያቄ መመለስን ታሳቢ አድርገው የተዋቀሩ ናቸው፡፡ የብዝኃነትን ጥያቄ ለመመለስ ፌዴራሊዝምን መከተል ብቸኛው አማራጭ ባይሆንም የተሻለው አማራጭ መሆኑ ግን በተለያዩ አግባቦች በየሃገራቱ እየተስተዋለ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የፌዴራል ስርአት መነሻና መድረሻ አምባገነንነትን ማስፈን ሳይሆን የተለያዩ የብሔር ቡድኖች ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩና በፌዴራል ተቋማት ፍትሐዊ ውክልና እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ ራስን በራስ ማስተዳደር ፖለቲካዊና የግዛት ነፃነት ማግኘት ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል የፌዴራል ተቋማት መሬት ላይ ያለውን ብዝኃነት ማንፀባረቅ እንዲኖርባቸው ማድረግ ነው፡፡ በቡድን ፎቶ ግለሰቦች ቀድመው የራሳቸውን ፎቶ እንደሚያዩት ሁሉ፣ የፌዴራል ተቋማቱ ውስጥ የተለያዩ የብሔር ቡድኖች ቀድመው የሚፈልጉት የቡድናቸውን ተወካይ ነው፡፡ ይህ የተቋማቱን ተቀባይነትም ይጨምራል፡፡ እነዚህ ቡድኖች በብሔራዊ ደረጃ የፖሊሲ አወጣጥ ላይ ተፅዕኖ የመፍጠር ዕድል እንዲያገኙም ስለሚያደርግ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ትሩፋት የሆነው ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ጥያቄ ላይ እንዳይወድቅ ይረዳሉ፡፡

እንደምናስታውሰው፣ ባሳለፍነው አመት በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች አለመረጋጋት አጋጥሞ ነበር፡፡ አንዳንዶች ይህንን መታወክ የፌዴራል ሥርዓቱ በአግባቡ እየሠራ ላለመሆኑ በማሳያነት  ያቀርባሉ፡፡ የዚህ ጽሁፍ መነሻም የማሳያውን ትክክለኛነት ማሄስ ነው።

በበርካታ መሥፈርቶች የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ጥያቄ ከመመለስና የፖለቲካና አስተዳደር አካላትን ከመገንባት አኳያ ብዙ ርቀት መጥተናል፡፡ ከ25 ዓመታት በፊት ዝቅተኛውን አገልግሎት ለመስጠት እንኳን የሚያስችል ተቋማዊ አቅምና የሰው ኃይል በሃገሪቱ ላይ ያልነበረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ አሁን ክልሎች ከሰው ኃይል አንፃር በአግባቡ የተደራጁ ናቸው፡፡ በተወሰነ መልኩ የገንዘብ አቅምም አዳብረዋል፡፡ ይሁንና ችግሮችም እንዳሉ ግልጽ ነው፡፡ ይሁንና፣ ባሳለፍነው አመት ሃገራችን  ለገጠማት ችግር መነሻው ፌዴራሊዝምን እንደ አዲስ የማኅበረሰብ ግንባታ መሣሪያ አድርገን አለመጠቀማችንን እንጂ የፌደራሊዝሙን ጦስ የማያመላክት እንደሆነ ብዙዎች ያረጋግጣሉ፡፡

ስኬታማ ፌዴሬሽኖች አዲስ ማንነት ለመፍጠር ፌዴራሊዝምን በአግባቡ ይጠቀሙበታል ሲሉ ከሚከራከሩት ምሁራን መካከል አንዱ የሆኑትና በጉዳዩ ላይ ከሪፖርተር ጋዜጣ ጋር ቃለ ምልልስ ያደረጉት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ተባባሪ ፕሮፌሰርና የፌዴራል ጥናት ማዕከል ሊቀመንበር ዶ/ር አሰፋ ፍስሃ ፦

*[. . .] የሆነ ቦታ ትወለዳለህ፡፡ የአንድ የሙያ ማኅበር አለያም ሃይማኖታዊ ቡድን አባልም ልትሆን ትችላለህ፡፡ ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነን፡፡ የተለየ የብሔር ማንነትም ይኖረናል፡፡ እነዚህን የተነባበሩ ማንነቶች እንዴት ማስታረቅ እንችላለን? በተገቢ ሁኔታ እየሠሩ ባሉ ፌዴሬሽኖች በተለያየ ደረጃ የተለያዩ ማንነቶች ይኖሩናል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ማንነቶች ሁሌም ይጋጫሉ ማለት አይቻልም፡፡ የብሔር ማንነትህን በአካባቢያዊ አስተዳደሮች ልትጠቀምበት ትችላለህ፡፡ ነገር ግን ሁሉንም የሚያቅፈው ኢትዮጵያዊ ማንነትም አለህ፡፡ ኢትዮጵያዊ ማንነት በሌሎች ማንነቶች ላይ ዋጋ በመክፈል የሚገኝ እንደሆነ ወይም የብሔር ማንነት ከሌሎች ሁሉ ማንነቶች በላይ እንደሆነ አድርጎ ማሰብ የተሳሳተ የፌዴራሊዝም አረዳድ ነው፡፡ በእኔ ዕይታ በተለያየ ደረጃ የሚገኘው የፖለቲካ አመራርም ይህን ተገንዝቦ ፌዴራሊዝምን በመጠቀም የተለያዩ ማንነቶች ያላቸው የተለያዩ ህልሞች ለማስታረቅ አልቻለም፡፡*

ሲሉ ፌደራላዊ ስርአቱ መፍትሂ እንጂ የችግር ምንጭ እንዳልሆነ በተጨባጭ ያረጋግጣሉ። *በፖለቲካ ቀውሱም ሆነ ከዚያ በፊት በነበረው ጊዜ ያየነው ሌላው ችግር ራስን በራስ በማስተዳደር ፅንሰ ሐሳብ ላይ የተሳሳተ ዕይታ መኖሩ ነው* ካሉ በመኋላ የፌደራላዊ ስርአቱን መፍትሂነት እንደሚከተለው ይገልፁታል፤

*ራስን በራስ ማስተዳደር በክልላዊ ወይም አካባቢያዊ የፖለቲካ ተቋማት መተዳደር ማለት ነው፡፡ የራስን ቋንቋና ባህልን መጠቀምንም ይጨምራል፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች ራስን በራስ የማስተዳደር መብትን ጎጥ ለመገንባት ሊጠቀሙበት ሲሞክሩ ይስተዋላል፡፡ ክልላዊ ብሔርተኝነት እያደገ በመጣበት ሁኔታ ይኼ አደገኛ ነገር ነው፡፡ ራስን በራስ ማስተዳደር ለሌላው ማንነት ክብር መስጠትና ማስተናገድም ጭምር ነው፡፡ በተለያዩ ማንነቶች መካከል ንግግርና ግንኙነት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡*

በሃገራችን ተግባራዊ የሆነው የፌደራል ስርአት የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ግንኙነት ተደጋጋፊ እንደሆነ የሚያጠይቅ ነው፡፡ አንዳቸው ያለ ሌላቸው አይኖሩም፡፡ አንዱ ክልል ቀውስ ሲኖረው ችግሩ የዚያ ክልል ብቻ ይመስለናል፡፡ ነገር ግን በፌዴሬሽን ውስጥ የአንዱ ክልል ችግር ሌሎች ክልሎችንና የፌዴራል መንግሥቱን መንካቱ የማይቀር ነው፡፡ በቅርቡ ኦሮሚያና አማራ ክልሎች ችግር በገጠማቸው ወቅት መጀመሪያ ማንንም ሳይጠብቁ ምላሽ መስጠት የነበረባቸው ክልሎቹ ራሳቸው ነበሩ፡፡ ለዚህ ደግሞ ፌደራላዊ ስርአቱ በህግ ያስቀመጠላቸው መብት ነበር። አለማድረጋቸው ደግሞ ባለስልጣናቱን እንጂ

ስርአቱን ሊያስኮንን የሚያስችል ተጠየቅ የለውም። ጉዳዩን ለዚህ ተረክ መነሻ ምክንያት ከሆነን ያሳለፍነው አመት ሁከት ስንመለከተውም ማረጋገጥ የምንችለው የፌደራላዊ ስርአቱን የመፍትሄ ምንጭ መሆን እንጂ ለተፈጠረው ችግር ምክንያት መሆኑን አይደለም። በኦሮሚያ ክልል ቀውሱ ለ11 ወራት ሲቀጥል የክልሉ መንግሥት ችግሩን ለመቅረፍ ምንም ዓይነት የፖለቲካ መፍትሔ አልሰጠም፡፡ በአማራ ክልልም ተመሳሳይ ነገር ነው የተፈጸመው፡፡ ስለዚህ በፌዴራል ሥርዓታችን የእነዚህን ተቋማት ተመጋጋቢነት ማየት አልቻልንም፡፡ ተቋማቱ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡም ይህ እምነት ያለው አይመስልም፡፡ ተቋማቱ የሚጠበቅባቸውን ሚና በወቅቱ ከመወጣት ይልቅ ገዥው ፓርቲ ምላሽ እስኪሰጥ ይጠብቁ ነበር፡፡ በሒደቱም በርካታ ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡ በርካታ ንብረትም ወድሟል፡፡ ይህ የሚያመላክተው ደግሞ ስርአቱ ያጎናጸፋቸውን ፖለቲካዊ ጸጋ መጠቀም ሳይችሉ በቀሩ አመራሮች እንጂ የፌደራላዊ ስርአቱን ተግዳሮት አይደለም፡፡

በአንዳንድ ጉዳዮች ሥርዓቱ የገባውን ቃል በተግባር ፈጽሟል፡፡ ለምሳሌ ሰፋፊ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ተካሂደዋል፡፡ ኢኮኖሚውም በአግባቡ እያደገ ነው፡፡ ነገር ግን በአስተዳደር ረገድ ክፍተቶች መኖራቸው የማይካድና ይህንኑ ለማስተካከልም መንግስት እየተጋ መሆኑ በሚታወቅበት አግባብ ስርአቱን የችግር ምንጭ አድርጎ መሞገት ምክንያታዊ አይሆንም ፡፡

ሕገ-መንግሥቱ መሬትና የተፈጥሮ ሀብቶችን የተመለከቱ ሕጎች የማውጣት ሥልጣን የፌዴራል መንግሥቱ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በፌዴራል ሕግ አማካይነት መሬት የማስተዳደር ሥልጣን የክልሎች እንደሆነም ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን በአንቀጽ 40 ላይ መንግሥትና ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የመሬት የጋራ ባለቤቶች እንደሆኑ ተደንግጓል፡፡ ራስን በራስ ማስተዳደር በራሱ ከመሬት ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ስለሆነም መሬትን የግጭት ምንጭ ወይም የፌደራላዊ ስርአቱ ችግር እንደሆነ የሚናገሩ ሃይሎች ቀድሞ ነገር መሬት የፌዴራል መንግሥቱና የክልሎች የጋራ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ አድርጎ ስርአቱ መፍትሄ እንደሆነ ማስቀመጡን ለረዱ ይገባል፡፡ በአፈጻጸም ላይ ለሚኖሩ ችግሮች በገዥው ፓርቲ ውስጥ ያሉና በየመንግስታዊ መዋቅሩ እንዲሁም የተቃዋሚ ፓርቲዎችን የሚመሩ ሃይሎችና በመሰል አደረጃጀቶች ውስጥ የመሪነት ስፍራውን የተቆናጠጡ ግለሰቦች እንጂ የፌደራላዊ ስርአቱ ነው ሊያስብል የሚችል አመክንዮ አለመኖሩንም እንደዛው። የፌደራላዊ ስርአቱን ድክመት ለማጠየቅ በሚነሱት የሰብአዊና

ዴሞክራሲያዊ መብቶች ረገድም ችግር አለ ከተባለ በተመሳሳይ የግለሰቦቹ እንጂ የስርአቱ ለመሆኑ አንዳች ማጠየቂያ ማቅረብ አይቻልም።

ከላይ እንዳልነው፣ ችግሮች መኖራቸው እርግጥ ነው። ልዩነቱ ችግሮቹ መታየት ያለባቸው በአስተዳደራዊ በደል እንጂ በፖለቲካ ወይም በርእዮተ አለማዊ ሊሆን ከአለመገባቱ ላይ ነው። በየዕለቱ ሕዝቡን የሚያጋጥሙ በርካታ አሰልቺ ነገሮች ስለመኖራቸው አምኖ እነዚህን ችግሮች ለማስወገድና የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት ጥረት እያደረገ የሚገኝን መንግስት ማገዝ ጤናማና ህዝብን ማእከል ካደረገ ተቃዋሚ ፓርቲ ቢጠበቅም ለዚህ ያልታደልን መሆናችን ስርአቱን የችግሮች ሁሉ ምንጭ የሚያደርግ ማህበረሰብ ቢበረክት ሊገርመን አይገባም፡፡ በብዙዎቹ መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ ሥራን በጥራት ከማከናወንና ውጤት ከማስመዝገብ ይልቅ፣ ያለምንም አሳማኝ ምክንያት ማጓተት በጣም የተለመደ በመሆን ላይ ነው፡፡ ‹‹እሺ›› ማለት ነውር ሆኖ ‹‹አይሆንም›› ማለት ይቀላል፡፡ የዚህ ችግር ባለቤቶች ደግሞ እሺ የማይሉት ብቻ ሳይሆኑ በአንድ በኩል ፌደራላዊ ስርአቱን የችግሮች ምንጭ እንደሆነ የሚያወሩና በሌላ በኩል ግን በእጅ መሄድን እንደህጋዊ አሰራር የሚወስዱት ነቸው፤ እንጂማ ፌደራላዊ ስርአቱ እነዚህ ችግሮች የማይፈጠሩበት ቢፈጠሩም ባግባቡ የሚፈቱበትን ስርአት ከመዘርጋት ጀምሮ ተቋማትንም ገንብቷል። እዚህ ላይ መኮነን ካለበት ሊኮነን የሚገባው በስርአቱና በተቋማቱ መጠቀም ያቃተው እንጂ ስርአቱ ሊሆን የሚችልበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

ሁሉም ማለት በሚቻል ደረጃ እንደሚስማሙበት፣ የፌደራላዊ ስርአቱ ከዚህ ቆሻሻ አስተሳሰብ የምንፋታበትን እና ከዘመናዊ አስተሳሰቦችና አሠራሮች ጋር በሚገባ ለመተዋወቅ የሚያስችለንን ስርአት ዘርግቷል፡፡ ከመዋዕለ ሕፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ድረስ ትልቅ ዋጋ በመስጠት እየተሰራ የሚገኘውም ስለዚህ ነው፡፡ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመብዛታቸውም ሆነ ጥራት ይኖራቸው ዘንዳ መለፋቱም ስለዚህ ነው፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመምህራን፣ በድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ በቴክኖሎጂዎችና በመሳሰሉት ተደራጅተው ከዘመኑ ጋር እኩል መራመድ የሚችሉባቸው አሰራሮች ተቀይሰው ወደተግባር የተገባው ከእንደዚህ አይነት የተሳሳተ አስተሳሰብ እንላቀቅ ዘንድ ነው፡፡ ለዘመኑ ጥያቄ ምላሽ መስጠት የሚችሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እየተገነቡ ያሉት ለዘመኑ ጥያቄ ምላሽ መስጠት የማይችል አመራር እንዳይኖር ነው ፡፡

እየተገነባ ያለው የፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ልማዳዊና አሳሪ የሆኑ አሠራሮችን ማስወገድ የሚያስችል እንጂ የሚያገነግን አይደለም፡፡ ሥራን በሚፈለገው ፍጥነትና የጊዜ ቀመር ውስጥ በጥራት ማከናወን የሚያስችል፤ ማጓተትንና ማደናቀፍን ደግሞ የሚያስወግድ። ሙስና የዘቀጠ ስብዕና ባላቸው በማይረቡ ሰዎች የሚፈጸም እንጂ ስርአቱ ያመጣው አይደለም፡፡

ስለሆነም ነው እየተገነባ ያለው ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የለውጥ አንቀሳቃሽ በመሆን በሕዝቡ ባህል፣ ልማድ፣ አኗኗር፣ አስተሳሰብ፣ መስተጋብርና በመሳሰሉት ዕመርታ እንዲኖር፤ የረቀቁ ቴክኖሎጂዎችን እንድናውቅና እንድንላመድ ያስቻለን፤ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን የለውጥ ሽግግር እንዲፋጠን፤ ከግብርና ኢኮኖሚ በማላቀቅ የኢንዱስትሪ ሽግግራችን እብንዲቀላጠፍ ያበቃው። በኅብረተሰቡ ውስጥ ለግጭት የሚዳርጉ አላስፈላጊ የርስ በርስ ሽኩቻዎችን በውይይትና በድርድር እንዲለዝቡ፤ ጭፍን ጥላቻዎችና በመረጃ ያልተደገፉ ጥርጣሬዎችን እንዲወገዱ ከማስቻሉም በላይ፣ በግልጽ የሚታዩ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በማቅረብ ሥልጡን ግንኙነቶችንን እንድናዳብር ያስቻለው፡፡ ባጠቃላይ፣ የኛ ፌደራል ስርአት ይህ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።